# <u>የተቀደሱ ፍልሚያዎች፡-</u>

( በዚህ ርዕስ ዐበይት የፍልሚያ ጽሁፎች ይቀርባሉ። የሚከተለው ርዕስ ቅደም-ተከተሉን ሳይዝ የቀረበው በአስቸኳይነቱ መኾኑን ሳንባቢያን በትህትና እገልጻለሁ )

## ለተቃዋሚ ፖለቲካ ቡድኖች

## እንኳን ለዘመነ-ማርቆስ በሕይወት አሸጋገራችሁ።ኖርን ካላችሁ!

የአገራችን ምዕራብ ከጎንደር እስከ ጋምቤላ ድረስ ወደ ውስጥ እስከ ፴ ኪሎሜትር የጠለቀ ለም መሬት የአገራችን ገበሬዎች እየተገፉ እየተዘረፉ እየታሰሩ እየተጉላሉ መቀማታቸውን ስንሰማ ከርመናል። አንጀት የሚበጥሰው ሊጥብቃቸው፡- ሊከላከልላቸው፡ ሊመክትላቸው የሚገባው ደመወዙን እየከፈሉት የሚያስተዳድሩት ወታደር የዚህ ወንጀል ተባባሪ መኾን ብቻ ሳይኾን በቀንደኝነት ፈጻሚ መኾኑ ነው።

አንድ ሰሞን ትንሽ ለመድመቅ የሞከረ የድምጽ ተቃውሞ ቢሰማም ገዥዎአቹ እያስተባበሉት ከሰመ። ጉዳዩን በባለጉዳይነት ከሚከታተሉት ሌላ ሕዝቡ አገር ሰላም ሊመስለው የሚችል ቢኖር አይፈረድም። ማን ቀስቅሶት! ማን አለሁልህ ብሎት? !
ይህን በተመለከተ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች በቅርቡ ድምጻቸውን ያሰሙ ወይም ያስነበቡ ካሉ አምልጦኛል። ኢሓፓ ግን መስከረም ፭ ቀን ፪ሺህ ፪ ዓ.ም. የሱዳንን መንግሥት ከኢትዮጵያ ግዛት ከጎንደር አስተዳደር ባስቸኳይ እንዲወጣ ጠይቋል። ምንም ጥያቄው ውስን ቢኾንም ከሌሎቹ የተሻል በመኾኑ ሊመሰገን ይገባዋል።

## ፍልሚያው!

## እንደምረዳው ፖለቲከኛነት ላፍ እንኳን ለሕዝብና ለአገር መቆም ነው። ተሳስቼ ከኾነ ልታረሙ! ካልኾነ ግን፡- ፖለቲከኞች ለአገር መቆምን ጀምሩት። አሳዩንም።

## የሱዳን የአገር አተዳደር ሚኒስትር፡ መስከረም ፯ ቀን ፪ሺህ ፪ ዓ.ም. ሱዳን ትሪቢዩን በሚባለው ጋዜጣ በሱዳንና በኢትዮጵያ ምካከል የድንበር መካለሉ መስከረም ፳፱ ቀን እንደሚጀምር ዐወጁ። ኢትዮጵያችንን የሚገዙት ግን ‘ጭጭ ምንጭጭ’ እንዳሉ ነው። ምን ይደነቃል።ለማንኛውም እናንተ የፖለቲካ መሪዎች አልሰማንም ልትሉ አትችሉም። ብትሉም ማንም አያምናችሁም። የሚያሳዝነው ግን

እናንተም እንደገዢዎቻችሁ 'ጭጭ…' ማለታችሁ ነው። ከኃላፊነትም አታመልጡም። ስለዚህ፦

ሀ) አገር ውስጥ ያላችሁት፦
   - ባስቸኳይ ተሰባስባችሁሕዝቡን ለሰላማዊ ሠልፍ ጠርታችሁ ዕውነቱን ማስረዳት ግዴታችሁ ነው።
   - ሳትነግሩት ቀርታችሁ፦ነገ በዚህ ምክንያት ጦርነት ሲነሳ ሕዝቡንና ልጆቹን ለጦርነት ተነሱ ብትሉ " ለምን?" ቢሏችሁ፦ ምን ትመልሳላችሁ?! ጸለቲከኞች እንኳን መልስ ታጣላችሁ ማለት ተላላነት ሳይኾን አይቀርም።
   - ርግጥ፦ የፖለቲካ ቡድኖች ሁላችሁም በአንድ መቆም እንደሚቸግራችሁ ይገባኛል። በጥቃቅን ነገር የምትለያዩት ግን እሱን ወደኋላ አድርጋችሁ በአንድ መሠለፍ የአባት አያቶቻችሁን ጋሻ ወደ ማንሳቱ ያቃርባችኋል። እነዚያኞቹ ይለይላቸው።

ለ) ውጭ አገር ያላችሁት ፖለቲከኞችም ይህን መንፈስ ተከትላችሁ ማድረግ የሚገባችሁን እንደምታደርጉ ተስፋ አለኝ። እዚህ ላይ ዲጋፊ መገናኛ ብዙዎችን ሁሉ ለዚህ ማዋል ቅድሚያ ቢሰጠው ሳይጠቅም ይቀራል?

ሐ) ኹላችሁም ግን ለተባበሩት መንግሥታት፦ ለአፍሪካና ለአውሮፓ ኅብረቶች እንዲሁም ለአረብና ለእስያ አገራዊ ድርጅቶች መጻፍ ብቻ ሳይኾን የሕዝብን ፊርማዎች በማሰባሰብ ለአካባቢያችን ሰላም መደፍረስና መተላለቅ ከዝምታ ርቀው ይኽን እሳት ሳይቀጣጠል በቅጠል እንዲያጠፉት እንረባረብ።

ጽሑፌ ድርቅርቅ ቢል ከአረረ አንጀት ከደበነ ቆሽት ከተበሳጨ መንፈስ መኾኑን ከመግለጽ አልፌ የማንንም የቅርታ አልጥይቅም።

ኢትዮጵያችንን እግዚአብሔር ይጠብቅልን

ኮማንደር አሰፋ ሰይፉ